# 8ኛው የኢትዮጵያውያን የአውሮጳ የእግር ኳስ ውድድር
# በ አምስተርዳም/ ሆላንድ በኢትዮ-ስዊስ አሸናፊነት ተጠናቀቀ!

ከ ምሥጢረ ኃይለ ሥላሴ

8ኛው የኢትዮጵያውያን የአውሮጳ የእግር ኳስ ውድድር ከሐምሌ 22-24 ቀን (29 አውጉስት 31 አውጉስት) ለሶስት ቀናት በደማቅ ሁኔታ ተካሂዶ ተጠናቋል:: ቀደም ሲል ፌደሬሽኑ ይሳተፋሉ ካላቸው ክበቦች መካከል የፊንላንድ ቡድንና ከአሜሪካም ይገኛሉ ከተባሉት ሁለት ክለቦች መካከል አንዱ ብቻ በመገኘቱ ውድድር የተካሄደው በ21 ክለቦች መካከል ነበር::

አንዳንድ ክለቦች ተጠናክረውና መልካም ዝግጅት አድርገው የቀረቡ ሲሆን በቁጥር ብዙ የማይባሉ መሳተፉን እንደ ድል የቆጠሩም ታይተውበታል የዘንድሮው ውድድር:: ትልቅ መሻሻል አሳይተዋል ከተባሉት ውስጥ ለፍጻሜው ግማሽ ያለፈው የኢትዮ ሮማ አንዱ ሲሆን ኢትዮ ሆላንድ- ኢትዮ ስዊዲን -ኢትዮ ሽቱትጋርት ና ኢትዮ ኮሎኝም ከነዞሁ ተርታ የሚደመሩ ነበሩ::

ለመጨረሻው ፍልሚያ ያለፉት አራት ቡድኖች ኢትዮ- ኮሎኝ ኢትዮ ሮማ/ ጣልያን ኢትዮ ስዊድንና የአምናው አሸናፊ ኢትዮ ስዊዘርላንድ ሲሆኑ, ኢትዮ - ኮሎኝ ከ ኢትዮ- ሮማ ተጫውተው ጥሩ ፉክክር ከታየ በኋላ ኮሎኝ 2 ለባዶ በሆነ ውጤት አሸንፎ ለዋንጫው ውድድር ሲያልፍ ስዊዲን ከስዊዘርላንድ ጋር እጅግ ማራኪና እልህ አስጨራሽ ፉክክር የታየበት ውድድር አድርገው በመደበኛው ጊዜ አቻ በሆነ ውጤት 3-3 በመሆናቸውና በተጨማሪውም ሰዓት አሸናፊው ሊወሰን ባለመቻሉ ወደ ፍጹም ቅጣት ምት መመራቱ የግድ ሆነ:: በዚህ ጨዋታ ላይ የስዊስ ቡድን 3-1 ሲመራ ቢቆይም ወደመጨረሻው ገደም ከፍጹም ቅጣት ምት ክልል ጠርዝ ላይ በተሰጠበት አላስፈላጊ የቅጣት ምትና ሌላ የፍጹም ቅጥት ምት ስዊድን አቻ ሆኖ ለልብ አንጠልጥሎ ፍጹም ቅጣት ምት (ሪጎሪ) ደረሰ::

መድረስ ብቻ ሳይሆን የመጀመርያዎቹን ምቶች ከመረብ አገናኝቶ ስዊሶች ደግሞ በተከታታይ ስተው 1-3 ከዚያም 2-4 ሆነው የስዊስ ደጋፊዎች ተስፋ በቆረጡበት ደቂቃዎች ውስጥ በረኛቸው "ጎሹ" በተከታታይ አድኖላቸው በአንድ ግብ ልዩነት ለዋንጫው ለማለፍ ችለዋል::

እዚህ ላይ በሁለቱ ቡድኖች መካከል በኳሱ ሜዳ ከሚደረገው ፍልሚያ ባልተናነሰ ሁኔታ ደጋፊዎቻቸው ቡድናቸውን ለማበረታታት ያደረጉት አስተዋጽኦ አልፎ አልፎም በግጥም መወጋጋቱ ለጨዋታው ብቻ ሳይሆን ለበዓሉም ውበትና ሞገስ ሰጥቶት እንደነበረ መጥቀሱ የግድ ይመስለኛል:: አምና ፈረንሳይ ውስጥ የታየው በዜማና ግጥም ቡድንን ማሞገስና ማበረታታት በአንጻሩ ተፎካካሪን ሸርደድ አድርጎ የማለፍ ለምሳሌም የተፎካካሪ ተጨዋቾች ቆሰልኩ ብሎ ወድቆ ሲንፈራፈር - "ውሸቱን ነው! እረ ውሸቱን ነው" እያሉ ዳኛው "አልተጎዳህም ተነሳ የሚል ምልክት ሲሰጥ "የገባው ነው! ዳኛው የገባው ነው! አራዳ ነው ዳኛው አራዳ ነው!!" ወይንም የማይገባና ተጨዋቾችን ሊጎዳ የሚችል አጨዋወት በተቃራኒ ላይ ሲቃጣ - " ሊገለው ነው! ልጁን ሊገለው ነው!!" በህብረት ዜማ ሲዜም ሌላው ወገን እንዲሁ አጸፋውን ሲሰጥ ውድድሩንም ሆነ ዓመታዊ በዓሉን የማይረሳ አድርጎት አልፏል::

በጉጉት የተጠበቀው የስዊስና የኮሎኝ ቡድን ጨዋታ እንዴት ይሆን? የኮሎኝ አማካይ በተለይም ጨዋታ ሰሪው (Playmaker) በአምላክን እንዴት መቆጣጠር ይቻላል የሚለውን የስዊስ ደጋፊዎች ስጋት የተጋሩ ያልመሰሉት ተጨዋቾች ወደ ሜዳው የገቡት በሙሉ ልብ ነበር:: ጥሩ ጨዋታና ጸባይ የታየበት ጨዋታ ባዶ ለባዶ እንዳሉ እረፍት የሚወጡ ቢመስልም ስዊሶች ጨዋታውን ተቆጣጥረው የ አንድ - ሁለት ቅብብል ስልታቸው ኮሎኞችን አደናግሯቸው እያለ በፈለቀ አማካይነት ከ20 ሜትር አካባቢ የተተኮሰ ከራራ ምት የበረኛውን የመወርወር ብቃት ከፈተነች በኋላ ከመረቡ ጋር ተገናኘች:: ስዊሶች ፈነደቁ : ደጋፊዎቻቸው ጉሮ ወሸባዬ አሉ:: የስዊሶች ጥቃት ቀጥሎ ሌላ ጎል ሳይደገም የዳኛው ፊሽካ የእረፍት ሰዓቱን አብስሮ በስዊስ አንድ ለዜሮ መሪነት እረፍት ተወጣ::

ከእረፍት በኋላ የውድድሩ ኮከብ ተጨዋች የሆነውን ሰሚርን ስዊሶች አስገብተው በሙሉ ኃይላቸው ፈጣንና ማራኪ የቅብብል ዜዴያቸውን በመጠቀም አከታትለው ሁለት ጎሎች አስቆጠሩ የድል አቅጣጫ በግልጽ እየታወቀ ባለበት ሁኔታ ስዊሶች ሌላ

ለጨዋታው አራተኛ የሆነችውን ግብ አስቆጥረው አራት ለባዶ መምራት እንደ ጀመሩ አዳዲስ ተጨዋቾች ተቀይረው ጨዋታው ቀጥሎ ኮሎኞች አንድ ጎል አስቆጥረው የዚህ ዓመት የአውሮጳ የእግር ኳስ ውድድር በስዊስ 4-1 አሸናፊነት ተጠናቋል::

የዚህ ዓመት የክብር እንግዳ የሆነው የቀድሞው የኢትዮጵያ ቡድን ተጨዋች የነበረው ንጉሴ ገብሬ ለአሸናፊው ለስዊስ ቡድን ዋንጫውን ሸልሟል:: ስዊሶች ዋንጫውን ሲወስዱ በተከታታይ ሁለተኛ ጊዜ መሆኑ ነው:: በፌደሬሽኑ ደንብ መሰረት ለሶስት ጊዜ ዋንጫውን የወሰደ ያስቀራል የሚለው ደንብ በሚቀጥለው ዓመት በስዊሶች አሸናፊነት ተግባራዊ ይሆናል የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም:: እንዳምናው ሁሉ የዚህ ዓመት ኮከብ አሰልጣኝ የስዊሱ አበበ :ኮከብ ተጨዋች ሰሚር ሆነው ተሸልመዋል:: ብዙ የስዊስ ተመልካቾች ከተዘጋጁት ዋንጫዎች መካከል የጸባይ ሊዘጋጁ ከሚገባቸው ደግሞ የ "ኮከብ ተመልካች"ም ለስዊስ በተገባ ነበር ይላሉ! አዎ! በሰላም በፍቅር ድጋፍ ገልጾ መለያየት የሚያሸልም መሆን አይኖርበትም የሚል ይኖርል? ብራቮ ስዊሶች!

በነገራችን ላይ የሚቀጥለው ዓመት ውድድር በሎንዶን ይደረጋል ሲል ፌደሬሽኑ ቢያስታውቅም ባለው የመግቢያ ፈቃድ የማግኘት ችግር ምክንያት ብዙ ሰው እንዳይገኝ ምክንያት ይሆናል የሚል ስጋት ከወዲሁ ይሰማል:: ፌደሬሽኑም መላ ይፈልጋል የሚል እምነት በብዙዎች ዘንድ መኖሩን በርካታ ሰዎች ሲነጋገሩበት ተደምጧል::

ቀደም ሲል ethiosports.com የየእለቱን ውጤት ለማቅረብ ቃል በገባው መሰረት ያደረገው ሙከራ በፌደሬሽኑና አዘጋጅዎቹ የሥራ ብዛት ምክንያት በወቅቱ መረጃዎች ማግኘት በለመቻሉ አልተሳካም:: ጠቅላላ ዝግጅቱን: ድክመቶችና ጠንካራ ጎኖችም ካሉ ዘርዘር ባለ መልኩ ሰሞኑን እናቀርባለን:: በዚህ ዓመት ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ተመልካች ነበር የሚል ግምት አለ:: በውል ለማወቅ ምንም አይነት መለኪያ ላይኖር ይችላል:: ሕዝቡ በብዛት የተገኘው መሻሻል በፌደሬሽኑም ሆነ በአዘጋጅ አገሮች ጥረትና መሻሻል ስለተደረገ ነው?

የሚልዮን ብር ጥያቄ ሊሆን ይችላልና በዚህና በተያያዙ የአምስተርዳምን ዝግጅት በሚመለከት እንመለስበታለን::

ቸር ይግጠመን!